4127 Redwood Rd.
Oakland CA 94610
(510) 530-3681

No 2029/2012
Date 11.02.2012

## በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፳፩ኛው መደበኛ ጉባኤ መግለጫ

በስደት ላይ የሚገኘውና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፳፩ኛውን መደበኛ ስብሰባ ከጥቅምት 21-23 /2005 ዓ/ም በኮሎምበስ ኦሐዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ካቴድራል አካሂዷል ።ጉባኤውም ወቅታዊ በሆኑ ዐበይት ጉዳዮች ላይ ተነጋግሯል፤ በውይይቱትም ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት፤ ስለ ሕገ ቤተ ክርስቲያን መከበር፣ ስለ መንበረ ፓትርያርክ ጽሕፈት ቤት መጠናከር ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት እንዲሁም እምነታችንና ታሪካችንን ለተከታዩ ትውልድ በቀጣይነት ስለማስተላለፍ ተወያይቷል።

ይልቁንም በአሁኑ ወቅት በብዙዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች አእምሮ ውስጥ ስለሚመላለሰው የቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት፥ በተለይም ቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ መንበራቸው ስለሚመለሱበት ሁኔታ ቅዱስ ሲኖዶስ በሰፊው ተነጋግሯል፤ ስለዚሁ የሰላምና የእርቅ ሂደት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ልዑካን በአካል ተገኝተው የሰላምና አንድነት ጉባኤውን መልእክት አድርሰዋል፤ ቅዱስ ሲኖዶስም ከቤተ ክርስቲያን ሰላምና አንድነት በላይ የሚያስቀድመው ነገር አለመኖሩን ገልጦአል፥ በአዲስ አበባ ያሉት አባቶች ቅዱስ ፓትርያርኩን ወደመንበራቸው እንዲመለሱ ከተስማሙ ቅዱስ ሲኖዶሱም አንድ፥ እረኛውም አንድ ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱም አንዲት ትሆናለች ብሎ ያምናል፤ ቅዱስ ፓትርያርኩም ወደ መንበራቸው ተመልሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን ኃላፊነት እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

ሕጋዊው ቅዱስ ፓትርያርክ በግፍ የተሰደዱበት እና ቅዱስ ሲኖዶሱንም ከምንም በላይ ሲያሳስበው የኖረው የቤተ ክርስቲያን አንድነትና የቀኖና ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ በመሆኑ በ፳፩ኛው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ተቀዳሚ አጀንዳ አድርጎ ሰፊ ውይይት በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ላይ በማድረግ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

1) በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ለሃያ አንድ ዓመታት ምዕመናንን ከምዕመናን፥ ካህናትን ከካህናት፥አባቶችን ከአባቶች መለያየቱ፥ ብዙዎቹን የቤተ ክርስቲያኒቱን እውነተኛ ልጆች አሳዝኗል። የቤተ ክርስቲያኒቱንም እድገትና ታሪክ በእጅጉ ጎድቶታል፤ ይህ አሳዛኝና አሳፋሪ ታሪክ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንዲወገድ የሰላም ደጁን ከፍቶ ሕጋዊው ቅዱስ

ሲኖዶስ በመጠበቅ ላይ ነው። ከዚህ አንጻር በአዲስ አበባ የሚገኙ ወገኖቻችንም እግዚአብሔር የከፈተውን የሰላም በር ተጠቅመው ወደ ከፋ ስህተት ቤተ ክርስቲያን እንዳያስገቧት ደግመው ደጋግሙ እንዲያስቡበትና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲዘጋጁ ጉባኤው ጥሪውን ያቀርባል፤

2) በአዲስ አበባ ከሚገኙት ሊቃነ ጳጳሳት መካከልም የተወሰኑት አባቶች በዚህ የልዩነት ታሪክ ላይ እንዳለን በሞት ማለፋቸው አሳዛኝ ሆኖ ሳለ፥ እኛ በሕይወት ያለነው ማስተካከል የሚገባንን ሳናስተካክል፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሳናስጠብቅ፥ ቤተ ክርስቲያንን አንድ ሳናደርግ ብናልፍ በሕይወት በሕዝባችን ፊት፣ በሞትም በእግዚአብሔር ፊት ተወቃሾች ያደርገናል። ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በጉባኤው ላይ እንዳለ በአዲስ አበባ ያሉት ጳጳሳት የፓትርያርክ ምርጫ ለማከናወን በዝግጅት ላይ መሆናቸውን በመገናኛ ብዙኃን መግለጫ መስጠታቸውን በሰማንበት ጊዜ በሰላምና አንድነት ጉባኤው ከተገለጸልንና ከሰማነው መልእክት ጋር የሚቃረን ሁኖ አግኝተነዋል፤ የተጀመረው የሰላም ድርድር መልክ ሳይዝ፥ ወደ ሌላ ፓትያርክ ምርጫ እንሄዳለን የሚለው ሀሳብ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በር ይዘጋል፤በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያውን ኦርቶዶክሳውያን በሙሉ ላለፉት 21 ዓመታት የነበረው የቤተ ክርስቲያን ልዩነት ተወግዶ ለማየት በታላቅ ተስፋ በሚጠባበቁበት ወቅት የምእመናንን ልብ ያሳዝናል፤ የቤተ ክርስቲያንንም ክብር ያዋርዳል። ስለዚህ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በአዲስ አበባ የሚገኙት ወንድሞቻችን ጳጳሳት ወደዚህ ቤተ ክርስቲያንን ወደሚከፋፍል ውሳኔ ከመድረሳችሁ በፊት ውሳኔያችሁ አንዲቱን ቤተ ክርስቲያን መፍትሔ በሌለው መንገድ የሚከፋፍልና ዳግመኛ መጥፎ የታሪክ ጠባሳ ትቶ የሚያልፍ እንዳይሆን በእርጋታና በዝግታ እንደገና ልታጤኑት ይገባል ይላል። በአንድ በኩል ለድርድር እንቀርባለን እየተባለ በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያንን እስከ አሁን ድረስ የለያየው ችግር መፍትሔ ሳያገኝ፥ በአንድ ዘመን በአንድ መንበር በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ላይ ሁለት አባት ለማስቀመጥና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጪ የሆነ ተግባር ለመፈጸም መዘጋጀት፥ አራተኛውና ሕጋዊው ፓትርያርክ በሕይወት እያሉ ሌላ ፓትርያርክ ለመሾም ማሰብ ፍጹም ተቀባይነት የሌለው ተግባር ነው። እስከ አሁንም የለያየንና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ያፈረሰው የቀኖና ቤተ ክርስቲያን አለመከበር ሆኖ ሳለ ቀኖናው ሳይከበር የሚደረገውን ምርጫ ፍጹም የማንቀበለው መሆኑንም ለመግለጥ እንወዳለን።

3) ምንም እንኳ እንዲህ ዓይነት አሳዛኝ ዜና ብንሰማም፥ ለሰላሙ ያለንን ዝግጁነት ለማሳየት፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የቀረበለትን ጥሪ ምክንያት በማድረግ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለአንድነቱ ይጠቅማሉ፤ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ያስጠብቃሉ ብሎ ያመነባቸውን የመነጋገሪያ አጀንዳዎች ቀርጾና ተደራደሪ የሰላም ልዑካንን ሰይሞ በተወሰነው ቀንንና ቦታ ለመላክ ወስኗል። ለዚህም የሰላም ሂደት መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአድባራትና የገዳማት አስተዳዳሪዎች፣ ምእመናን በሙሉ፥ በጸሎት ለሰላሙ መሳካት ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን ያቀርባል።

4) ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነትና ለቀኖና ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ እንዲሁም ለቀጣዩም ትውልድ አንዲት ቅድስት አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ለማስረከብ፥ ከታሪክ ተጣያቂነትም ለመዳን ፥ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወደመንበራቸው መመለስ አማራጭ የሌለው ብቸኛው መፍትሔ ነው ብሎ ቅዱስ ሲኖዶስ ያምናል፤ በመሆኑም ይህ ያለእርቅና ሰላም የሚሆን የፓትርያርክ ምርጫ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለዘላለም በማይፈወስ መልኩ የሚሰብር

የቤተ ክርስቲያናንን ልጆች አንገት የሚያስደፋ ስለሚሆን በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ የምትገኙ አበው ካህናት ገዳማውያን መነኮሳት እና ለቤተ ክርስቲያናችሁ የቆማችሁ የቅዱሳን ልጆች የሆናችሁ አባቶችና እናቶች ወንድሞችና እህቶች ሁላችሁም በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንድታመለክቱ፥ ይህን በታሪክ አሳዛኝ የሆነ ድርጊት ለማከናወን የተዘጋጁ ጳጳሳት ወደስህተት የማይገቡበትን መንገድ የሚያመለክትና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያስጠብቅ ድምጻችሁን እንድታሰሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በኢትዮጵያ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትም ለዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መለያየት ምክንያት ከመሆንና በታሪክም ከመወቀስ የሚያድን ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል ብለን እናምናለን። ይህም የሚሆነው የቤተ ክርስቲያኒቱን የወደፊት የአንድነት አቅጣጫ መወሰን የሚችሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ማለትም ሊቃነ ጳጳሳቱ፥ ካህናቱና፥ ምዕመናኑ ብቻ ስለሆኑ፥ መንግሥት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርግ ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል።

5) በዚህ ባለንበት በዩናይትድ ስቴትስ ግዛት በተፈጥሮ ማዕበልና አውሎ ነፋስ አደጋ ህይወታቸው ስላለፈው ና ከቤት ንብረታቸው ስለተፈናቀሉት አሜሪካውያን ወገኖቻችን ሐዘኑን በመግለጥ ቅዱስ ሲኖዶስ በጸሎት አስቦአቸዋል። ሕዝበ ክርስቲያንም በአደጋው ለተጠቁት አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያደርግ ጥሪውን ያቀርባል።

6) ቅዱስ ሲኖዶስ በስደት ያሉትን ምእመናን በተጠናከረ መንገድ ማገልገል ይቻለው ዘንድ የካህናት ማሰልጠኛ እንዲቋቋም፥ አብያተ ክርስቲያናት በወጥነት የሚተዳደሩበት ሕገ ቤተ ክርስቲያን የሀገሩን ሕግ በጠበቀ መልኩ እንዲጠና፥ የየአህጉረ-ስብከቶች መዋቅር እንዲጠናከር፥ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ እንዲሁም ተተኪ ትውልድ የሚፈልቅባቸው የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲጠናከሩ ውሳኔዎችን አስተላልፎአል። በመላው ዓለም ያሉት አህጉረ ስብከቶች ለሐዋርያዊ አገልግሎት በሚያመች መንገድና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጣቸውን ባገናዘበ መልኩ እንዲደራጁ በመወሰን ለተግባራዊነቱ ኮሚቴ ሰይሟል፤

7) የታላቁን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቅና ባለውለታ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውን እረፍት ቅዱስ ሲኖዶስ በታላቅ ሐዘን በጸሎት በማሰብ፥ እረፍታቸውን ምክንያት በማድረግ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ወስኖአል።

8) የሰላምና አንድነቱን ጉባኤ ውጤት አይቶ የቤተ ክርስቲያንን የወደፊት ጉዞ ለመወሰን በሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያምና ቅድስት ማርያም አብያተ ክርስቲያናት አስተናጋጅነት የሲኖዶሱ ልዩ ጉባኤ ከጥር 7-9 2005 ዓ/ም በሎስ አንጀለስ እንዲደረግ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል።

9) በመጨረሻም የኦሀዮ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሰላማ የኮሎምቦስ ኦሐዮ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ካህናት ምእመናን ለአስራ ሰባት ዓመታት ያለማቋረጥ ስለሚያደርጉትና ስላደረጉት አቀባበልና መስተንግዶ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በታላቅ አክብሮት ምስጋና በማቅረብ እንዲሁም ዛሬ በሕይወተ ሥጋ የሌሉትን የታላቁን አባት መልአከ ሰላም አባ ሰሎሞን ደሳለኝ መንፈሳዊ አደራ በመጠበቅ የደብሩ ካህናትና ምእመናን ያሳዩትን እርአያነት በማድነቅ ጉባኤው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎትና ቡራኬ ተጠናቋል።

ጥቅምት ፳፫ ቀን ፳፻፭ ዓም ኮሎምቦስ ኦሐዮ።

THE HOLY SYNOD OF THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHDO CHURCH